# እንኳን ለኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር የምስረታ በዓል አደረሳችሁ አደረሰን!!!

የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ጥቅምት 7 1993 ዓም የወያኔው አፋኝና ከፋፋይ ስርዓት በሰላማዊ መንገድ የስልጣን ሽግግር እንደማያደርግ ቀድሞ የተረዳና ለስልጣን በበቃበት የነፍጥ ትግል መውረድ አለበት ሲል ፊት ለፊት ለመፋለም ቆርጦ የተነሳ ፈር ቀዳጅ ድርጅት ነው።

የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ነፍጥ አንስቶ በረሃ ሲወጣ ዋና ዓላማው አገራችንና ህዝባችን በነፍጥ ሃይል አንባገነንን አውርዶ በነፍጥ ሃይል የሚገዛት አንባገነን ቡድን አያስፈልጋትም፡ ይህንንም ተግባራዊ ማድረግ የሚቻለው የአባት አያቶቻችን የአርበኝነት አርማ አንስቶ ለአገርና ህዝብ ሻማ ስንሆን ብቻ ነው በሚል " አንድነት ሃይል ነው" የሚል መሪ መፈክር አንግቦና የኢትዮጵያን ባንዲራ ትከሻው ላይ ተሸክሞ አፋኙን የወያኔ ቡድን ለመፋለም ተነሳ! ባደረገው ተጋድሎም እርስ በርሱ እንዲባላና አሁን "ለውጥ" የተባለው ክስተት እንዲፈጠር የአንበሳውን ድርሻ ድርጅታችን ይወስዳል ብንል ማጋነን አይሆንም።

ምክንያት ከ18 ዓመታት በላይ ያደረግነው ተጋድሎና የከፈልነው የጊዜ የአካልና የህይወት ዋጋ ዛሬ የስልጣን ጥማቸውን ሊያሳኩ በሚያጎነብሱ አካላት ሊጠልፉት ቢምክሩም፡ የለውጥ ሃይል የተባለውም በፍቅራቸው ወድቆ የአርበኝነት ዋጋችንን ሊያጣጥለው ቢሞክርም የከፈልነው በአርበኝነት ስለሆነና አርበኛ ደግሞ ዋጋ ስለማይጠይቅ የሚጸጽተን ነገር ባይኖርም በትግሉ ወቅት ያለቀባሪ የቀሩ ጓዶቻችንን ታሪክ ግን ማዳፈን እንደማይችሉ የምናሳይበት ግዜ ሩቅ እንደማይሆን አርበኝነትን ጠንቅቆ በሚያውቀውና ወገናችን ድጋፍ እውን እንደምናደርገው እርግጥ ነው።

በመሆኑም ዛሬ "ለውጥ" አለ በተባለበት ማግስት የራሱን አጥር አጥሮ በዘረፈው ሃብት እርስ በርሳችን እያጫረሰን ያለውን እኩይ ቡድን ሁኔታ ስናይ የከፈልነው ዋጋ የሚጸጽተን ሳይሆን ትግሉ እንዳላለቀ አመላካች መሆኑን ተረድተን ወደፊትም በህይወት ያለነው አርበኞች ለአገራችንና ህዝባችን መክፈል ያለብንን ዋጋ የምንከፍል መሆናችንን እየገለጽን ህዝቡ ድጋፍ እንዲያደርግልን በዚሁ አጋጣሚ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

በአሁኑ ወቅት በሸዋ ፡ በጎንደር፡ጎጃም፣ በወሎና የተለያዩ አካባቢዎች ለተፈጠረው እልቂት ሃላፊነቱን ህወሃት ይወስዳል ይህንንም ሃይል ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለማንበርከክና በሃይል የወሰዳቸው የወልቃይት፡ የራያና የመተከል መሬቶች ለማስመለስ በሚደረገው ተጋድሎእስከ ዛሬዋ ዕለት እየከፈልን ሲሆን፡ በቀጣዩም ከፋኖና ከህዝባችን ጎን የምንቆም መሆናችንን እያስታወቅን ለማይቀረው ተጋድሎ በአንድነት እንነሳ እያልን ፡ ለታጋይ ጓዶቻችንና ደጋፊዎቻችን በድጋሚ እንኳን ለኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር የምስረታ ዕለት አደረሳችሁ እንላለን።

የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር

ጥቅምት 7 2012 ዓም

ባህርዳር